# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ልዩ ዕትም መስከረም 2007 ዓ.ም.


## ዛሬም መሬት ለአንተ ለአራሹ

በካብ ላይ ብሰራ እባቡ መከራ

በዛፍ ላይ ብሰራ አሞራው መከራ

በምድር ብሰራ እረኛው መከራ

የት ውዬ የት ልደር ( ወፍ)

የኢትዮጵያ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የሚደርስባችሁ ጭቆናና ምዝበራ ዛሬም እንደ ትላንቱ እንደቀጠለ ይገኛል፡፡ የተለወጠ ወይም ደግሞ የተቀየረ ነገር ቢኖር አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ጨቋኞቻችሁና ረጋጮቻችሁ ከጉልተኛው ሥርአት ጭቃ ሹሞችና ምስለኔዎች ወደ ወታደራዊው ደርግ ጭቃ ሹሞችና ምስለኔዎች ባሁኑ ዘመን ደግሞ ወደ ዘረኛ አምባገነኖች ጭቃ ሹሞችና ምስለኔዎች መቀየራቸው ነው።

አርሶ አድሩ ወገናችን ስቃይህና መከራህ በብሩት ይሰማናል። የዛሬ 50 ዓመት ግድም በዘመኑ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተብሎ ይጠራ በነበረው ተቋም ተማሪዎች የነበሩ እንግልትህንና ጉስቁልናህን በመረዳት መሬት መሬት ለአራሹ ሊሰጠው ይገባል በላቡ ያስተማረው ይሚገትለታል! በማለት ያሰሙት መፈክር በመጀመሪያ በአገር አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ አብይና የእንቅስቃሴው እምብርት ለመሆን የበቃ መሆኑ ቢታወቅም እየዋለ እያደረ አጠቃላይ ለዴሞክራሲ፣ ለፍትህ፣ ለእኩልነትና በአጠቃላይ ለህዝባዊ መንግስት መመስረት የሚደረገው እንቅስቃሴ የማዕዘን ጥያቄ በመሆን እስከ ዛሬ በሀቀኛ የፖለቲካና ህዝባዊ ድርጅቶች ሲስተጋባ ይሰማል፡፡

ይህን ህዝባዊ ጥያቄ ይዘው የተንቀሳቀሱ ተገድለዋል፤ ተቃጥለዋል፤ ታስረው ተገርፈዋል፤ከሀገር ተሰደዋል። በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች አርሶ አደሮች ባካሄዱት የሙብት እንቅስቃሴ በጅምላ ተረሽነዋል፤ታስረው

ተገርፈዋል፤ ጎጇቸው ውስጥ እንዳሉ ተቃጥለዋል፤ ጎተራቸው ተመዝብሯል፤ ከብቶቻቸው ተነድተዋል፤ ሚስቶቻቸውና ሴት ልጆቻቸው ተደፍረዋል፤ ሰብላቸው በማሳ ላይ በእሳት ተቃጥሏል፤ ወንድ ልጆቻቸው ሲያርሱ ወይ ከብት ሲያግዱ ታፍነው ተወስደዋል፡፡ በልማት፣ በሰፈራ ወይም በሌላ ስም ከመኖሪያቸውና ከሚያርሱት መሬት ላይ ካለውዴታቸው ተፈናቅለዋል፡፡ ዛሬም በወያኔ የጎሳ ፖለቲካና ለም የእርሻ መሬትን ለድንበር ዘለል የባእድ የእርሻ ኩባንያዎች በመሸጥ በተለያዩ አካባቢዎች አርሶ አደሮች ከገዛ ወንዛቸው ከገዛ አገራቸው እየተፈናቀሉ ነው፡፡ ከተቃዋሚዎች ጋር አብራችኋል በሚል በተለያዩ አካባቢዎች በወያኔ ምስለኔዎች እየታሰሩ ይገረፋሉ፤ ሰቆቃ ይፈጸምባቸዋል፡፡ እስከ ዛሬ የአንተን ስም እያነሱ ያኔም አሁንም ጥቂት አጉራ ዘለሎች ከበሩ፡፡ አንተ ግን በነሱ ጫማ ተረግጠህ ከጉስቁልና አረንቋ መውጣት ተስኖህ መከራህ ከያኔው ብሶብህ አመት ወጥቶ አመት በገባ ቁጥር ኑሮህ ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ በስቃይና በችግር መኖር ግዴታህ ሆነ። በሀገርህ በመንደርህ የዜግነትህን መብት አጥተህ፣ በሰው ልጅነትህ ተፈጥሮ ያጎናጸፈችህና ማንም ሊነሳህ የማይችለውን የመናገር፣ የማሰብ፣ የመምከር የመማከር መብቶችህን ተነፍገህ መኖር ተገደድክ። የምትሻውን፤ የሚበጅህንና የወደድከውን መሪ፣ አስተዳዳሪዎችን፣ ዳኞችን፣ ወዘተ... በኃላፊነት ላይ የማስቀመጥ፤ የማውረድና የማስወገድ መብትህን በወያኔ ተነጠክ፡፡

በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመንም ሆነ የዛሬ 23 ዓመት የተወገደው የወታደራዊው ደርግ መንግስት በጦርነትም ሆነ በሰላም ወቅት የሀገር አለኝታነትህን፣ የወገን መከታነትህንና የኤኮኖሚ ዋልነትህን ሲዘክሩ ባጅተው አልፈዋል፡፡ ዛሬም ወያኔ የሚምለውና የሚገዘተው በአንተው ስም ነው፡፡ ሦስቱም አረመኔ ሥርአቶች ስምህን የፖለቲካ ሥልጣናቸውን ለማራዘሚያ ተጠቀሙበት እንጂ ለአንተ የበጀህ ወይ የተረፈህ አንዳች ነገር አልነበረም። ዛሬም ተጨማሪ በደል ደረሰብህ እንጂ ከመርገም ውጪ ቅንጣት ስንኳን በረከት አልተረፈህም፡፡ ዛሬ አፍ በፈታህበት ቋንቋ ማንነትህ እየተፈረጀ መድሎ ይጣልባሀል፡፡ ግፍ ይፈጸምበሀል፡፡ ሳትወድ በግድ አሳርህን የሚያሳይህ የወያኔና የአባሪዎቹ አባል እንድትሆን ትገደዳለህ፡፡ አባልነቱን ከተቃወምክ የእርሻ መሬትህ ይቀነሳል፡፡ ውሎ አድሮም ይወሰዳል፡፡ የዜግነት መብትህን ማለትም በሀገርህ ላይ አርሰህ፣ ምርትህን ሰብስበህ የመሸጥ የመለወጥ መብትህን ዛሬም እንደ ትላንቱ በጠበንጃ ተገፈሀል፡፡ ከወታደራዊው ደርግ ሥርአት በከፋ መልኩ ተሸማቀህ በፍርሀትና በመሸበር ለመኖር ተገደሀል፡፡ ያላመንክበትንና ያልፈቀድከውን እንድትልና እንድትናገር፣ እሺ በጄ እያልክ አንገትህን ደፍተህ እንድትኖር በአምስት ለአንድ በተሰኘው የወያኔ የስለላ መረብ ተጠርንፈህ እንድትኖር ተፈርዶብህ አሳርክንና መከራህን እያየህ ነው፡፡

በገዛ ጎጆህ ስለ መብትህ፣ እየደረሰብህ ባለው ስቃይና መከራ፣ ስለተጫነብህ የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ዕዳ፣ ስለታከተህና ስለሰለቸህ በወያኔ ካድሬዎች አታካች ስብሰባ ማውጋትና መምከር እንዳትችል ታግደሀል፡፡

ዛሬም ይርበሀል፣ ግና በእጅ ጣት የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ገንዘብ አከማቹ በሚል በጉስቁልናህ፣ በረሀብህና ጥምህ ይሳለቁብሀል፡፡ አያትክን፣ አባትክን እያንገበገቡ ደማቸውን ይመጡ የነበሩ ቱሀኖች፣ ቅማሎችና ቁንጮች ዛሬም መልካቸውን ብቻ በመቀየር የአንተንና የቤተሰብህን ደም ወግመው ይመጣሉ፡፡ በየጊዜው በአካባቢህ የተሾሙብህ ምስለ ወያኔዎች በማያቋርጥ መልኩ ለመንገድ፣ ለምንጭ ማጎልበት፣ በየብሔረ ሰቡ ለተሰየሙት ልማት ድርጅቶች፣ ለተለያዩ የወያኔ ድግሶች፣ ለአባይ ግድብ የግዴታ ውዴታ መዋጮ ትከፍላለህ። ኑሮህ እየመረረ እያንገፈገፈህ በመሄዱ ሞትን ደጋግመህ ትመርጥና ምላጭ መዋጥ ትመኛለህ። በገዛ አገርህ እንደ ባለ አገር የመኖር መብትህን በጠብመንጃ ጉልበት ተገፈሀል፡፡

አንተ ከአያቶችህና ከአባቶችህ የወረስከው አርበኝነትን፣ አይበገሬነትን፣ ጀግንነትን ነው፡፡ አገርህ መንደርህ የወንዝህ ሰዎችና ዘመድ አዝማዶችህ ተከብረውና ታፍረው መኖር የተቻላቸው አባቶችህ አጥንታቸውን ከስክሰው፣ ደማቸውን አፍሰው የኢትዮጵያንና የህዝቧን ጠላቶች በመመከታቸው ብቻ ነው፡፡ ከቀየህና ከጎጆህ የሚያፈናቅልህ፣ ለሰው ልጅነትህ ተገቢውን ክብር የሚነፍግህ፣ አንተ እንደፈቀድከው፣ እንዳመንክበት ሳይሆን የገዥዎችን እምነትና አመራር ተቀብለህ ጭጭ ምጭጭ ሳትል አንገትህን ደፍተህ ተገዛ ብሎ የሚያንገላታህና ግፍ የሚውልብህ እሱ ጠላትህ ነው፡፡ ጠላት ሁሌ ድንበር ጥሶ የሚመጣ ሳይሆን አጠገብህ ጉያህ ሥርም አለና ነቅተህ ወዳጅና ጠላትህን መለየቱ የግድ ይለሀል፡፡ ስለ አንተ በየዘመኑ የተነሱና በአናትህ ላይ የነገሱ አንተ የሀገርህ ኢትዮጵያ የኤኮኖሚ ዋልታ የኢትዮጵያ ህዝብ የወገንህ አለኝታ መሆንህን እያስረገጡ የሚመሰክሩ ቢሆንም በተግባር ግን ይረግጡሀል፣ ይጨቁኑሀል፣ ይዘርፉሀል፣ ይገርፉሀል፣ ከመሬትህ ከቀየህ ይነቅሉሀል፣ ያስሩሀል፣ በሰቆቃ ያሰቃዩሀል፣ ይገድሉሀል፣ ደምህም ደመ ከልብ ሆኖ የቀራል፡፡ አገርህ ኢትዮጵያ ድንግል ኢትዮጵያ እንዳልተባለች ሁሉ በዚህ ዘመን ልጆችህ ነን የሚሉ የእናት ጡት ነካሾች ፈልተው ማዕድኗን ዘርፈው ለባዕዳን አሳልፈው በመስጠት እያስበዘበዙ ነው፡፡ ይህ ሀብት የጥቂት አጉራ ዘለል ዘረኞች ብቻ ሳይሆን ያንተ የዘጠና ሚሊዮኑ ገበሬም ጭምር ነው፡፡ አንተ ግን የደሆች ደሀ፣ የጉስቁሎች ጉስቁል ነህ፡፡ ችጋርና ደዌ ይፈራረቁብሀል፡፡ አመት ወጥቶ አመት ሲገባ ግብር ይጨምሩብሀል፡፡ አንተ ግን የቤተሰብህንና የራስክን ረሀብ የምትከላባበት አቅም ተስኖህ የሸማግሌዎችህ አንጀት ብቻ ሳይሆን ያንተም አንጀት በጉርምስናህና በጉልምስናህ ተጨማዶ፣ የሌሊቱን ብርድና ቁሩን የምትከላከልበት ፣ የቀኑን ሀሩርና ቁሩን የምትቋቋምበት፣ የረባ ጨርቅ የለህም፡፡ እግሮችህን ከአሜከላ፣ ከእሾህ፣ ከእንቅፋት መከላከያ ከጎማ የሚሰራው የበረባሶ ጫማ እንኳ የለህም፡፡ ዛሬም መኝታህ መደብ ወይም ቆጥ እላዩ ላይ የምታነጥፈውም ያውም ከተገኘ ቁርበትና ሰሌን ነው፡፡ ዛሬም የምታርሰው በመቀናጆ ወይም በሬ ተከራይተህ ነው፡፡ ወያኔና አጫፋሪዎቹ ግን አድገሀል፤ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ይዘሀል እያሉ መራር ስላቅ ይሳለቁብሀል፡፡ በመከራህ ቁስል ላይ ጨው ይነሰንሳሉ፤ የመከራህን ቁስል በስንጥር ይጨቀጭቃሉ፡፡ መንግስት ቢለዋወጥ ምርጫ የሚሉት የልጆች ጨዋታ

ቢካሄድ የአንተ ህይወት ከምጣዱ ወደ እረመጡ ሄደ እንጂ ቅንጣት የተረፈህ የለም፡፡ ዛሬ ሰላም ስላለ በወታደርነት አንተ ወይም ልጆችህ እየተመለመሉ በጦር ሜዳ እንደማይረግፉ ገዢዎቹ ወያኔዎች በየጊዜው ቢለፈልፉም ከቀየህ ሶማሌ አዝምተዋቸው ጭዳ ሆነው የቀሩ እጅግ በጣም ቡዙ መሆናቸውን ለአንተ ለቀባሪው ማርዳት ነው፡፡

ግብር ትከፍላለህ ግና በዜገነትህ ማግኘት የሚገባህን ተነፍገሀል፡፡ በግብረ ሰናይ ድርጅቶች የውሀ ጉድጓድ ቢቆፈርም ወይ ውሀው ደረቀ ወይ ደግሞ የሆነ ብልሽት ደረሰበት ተብሎ እንዲሁ እንደ ሀውልት የተገተረው ብዙ ነው፡፡ በዜግነትህ የሀገርህ መንግስት ንጹህ ውሀ እንድታገኝ የማድረግ ግዴታ ነበረበት፡፡ የወያኔ ዘረኛ መንግስት ጠላትህ ነውና አንተን የሚጎዳ እንጂ የሚረባህን ለማድረግ ለመማሰን ባህርዩ አይደለም፡፡ በመንደርህ ህጻንት ይወለዳሉ ግና ከሚያድጉት በሞት የሚነጠቁት ይበዛሉ፡፡ እናቶች ከወሊድ ጋር በተያያዘ ሰበብ ይታመማሉ፤ ይሰቃያሉ ፤ ይሞታሉ፡፡ አንዳንዴ በሽተኛውን ሀኪም ቢያየውም አስፈላጊ ምርመራ የሚካሄድበት እሩቅ በመሆኑ በአብዛኛው በሽተኛው ሳይደርስ ከመንገድ ላይ ያርፋል፡፡ የምርመራው ክፍያም ከአቅምህ በላይ በመሆኑ ወይ ተበድረህና ተለቅተህ ከተመረመርክ በኋላ የመድሀኒት ዋጋ እጅግ ውድ በመሆኑ እያነባህ ወደ ጎጆህ ተመልሰህ የሞትክን ቀጠሮ ትቆጥራለህ፡፡ በሀገርህ የመታከም መብት ቢኖርህም በአምባ ገነኖች ተገፎብሀል፡፡ ልጆችህ አንጀት እርቋቸው ከሦስት ሰአት በላይ ተጉዘው ለመማር ስለተሳናቸው ከብቶች እያገዱ በወላጆቻቸው የመሀይምነት እግር ለመተካት ተፈረዶባቸዋል፡፡ ግና በዜግነትህ ልጆችህን የማስተማር ግዴታ የሚወድቀው ከአንተ ግብር በሚሰበስበው በዘረኛው ወያኔ ላይ ነው፡፡

የመሬትን ጉዳይና ጥያቄ አስመልክቶ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላ፤ አርሶ አደሩም ሆነ አርብቶ አደሩ ደግሞ በተለይ የሚመለከተው ከብዙ ፍርጆች አኳያ ነው። መሬትን ከሰብልና ከምጣኔ ሀብት ብቻ በመፈረጅ ብቻ አይረካም። ለመሬት ያለው ዕይታና ፍላጎት፤ ጠቀሜታና አገልግሎት፤ ስብልን በመሰብሰብና እንስሣትን በማርባት በቻ አይወሰንም። ለአንተ ለአርሶ አደሩ መሬት፤ የጎልውናህ መገለጫ፤ የማንነትህ መለያ፤ የሰብዕናህ ማስከበሪያ፤ የዜግነትህ ማረጋገጫ፤ የታሪክህና የባኅልህ መተርጎሚያም ጭምር መሆኑ ግልጽ ነው። መሬትና ሀገር፤ ሕዝብና ታሪክ፤ ባኅልና ዕምነት፤ ነጻነትና ኅልውናን ተጣምረው የሚያያዙበት በመሆኑ፤ መሬት ለአራሹ የተባለው ሕዝባዊ ጥያቄ፤ እስካሁን ድረስ ሁነኛ መፍትሄ አለማግኘቱ አያስደንቅም።

መሬትን አስመልክቶ፤ የአርሶ አደሩ ጥያቄ፤ ከሥነአዕምሮና ከባኅልም ጋር የተየያዘ ነው የሚባለውም፤ መሬትን በባለቤትነትና በርስትነት በመያዝ ብቻ የሚወሰን ባለመሆኑ ጭምር ነው። አርሶ አደሩ፤ መሬቱን፤ ዘመን ቆጥሮ፤ የዘምድ ግንድ ጠቅሶ፤ የትውልድ ተዋረድ ሀረግን መዝዞ፤ የሀገር ጠርፍና ድንበርን ከልሎ

የሚያይበት አድማሰ -ሰፊ የሆነ ቋሚ አመለካከትና ግንዛቤ አለው። ታሪካዊ ኩነቶችን፤ ሃይማኖታዊና ሌሎች ቅዱሳን መካናትን፤ ህያውነታቸው የሚከሰተው፤ በመሬት መከበር ነው። መሬት እንደ ግዑዝ ብቻ ሳይሆን፤ እንደ ዘለዓለማዊ ተቋም ( ኢንስቲትዩሽን ) የሚቆጠረውም፤ ህያው ከሆነው የሀገሪቱ ነዋሪ ጋር ዘመን በማይሽረውና ዕድሜ ከማያጠወልገው ከትውልድ ትውልድ ከሚሸጋገረው ታሪክ ጋር ስለተቆራኘ ነው። ጦርነት የተካሄደባቸውን ቦታዎችን በመጥቀስ ዝከረ- ታሪኮችን ለማስታወስ፤ መሬት ለያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ እንደ መሠረታዊ አፅመ- ርስቱ ይቆጥረዋል። የኣያት-ቅድመ አያት፤ የዘር ማንዘር፤ ሁሉ ማመሳከሪያውና ማገናዘቢያውም ጭምር ነው። አባቶቼ የወደቁበት ቦታ እያልክ የምትኮራበት ፤ አያት ቅድመ-አያቴ የተቀበሩበት፤ ልጆቼን አሳድጌ የዳርኩበት እያልክ በሐውልትነት ልትመለከት የምትችለው፤ መሬት በርስትነት ይዞታ ሲያረጋግጥልህ መሆኑ አሌ የሚባለበት አይደለም።

ስለሆነም የአንተ የአርሶ አደሩ ጥያቄ መልስ አላገኘም የሚባለውም፤ ይህን ፈርጀ ብዙ መስተጋብር ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ከሀገሪቱ ሕዝብ ሰማንያ አምስት ከመቶ (85%) የሚገመተው የሚተዳደርው በግብርና ኑሮ በመሆኑ፤ የአርሶ አደሩን መሠረታዊ ጥያቄዎች መፍታትና ሁለንተናዊ ዕይታን ያከተተ የመሬት ፖሊሲ በሥራ መተርጎም አርሶ አደሩ በነፃነቱና በፍላጎቱ የሚመሰርተው ሕዝባዊ መንግሥት ተቀዳሚ ተግባሩ መሆን አለበት የምንለውም በዚሁ ምክንያት ነው። ይህ ስኬታማ ሆኖ ባለመገኘቱ ነው ቀድሞ የነበረውም ሆነ በአሁኑ ወቅት በወያኔ አጋፋሪነት ተግባራዊ ሆኖ የሚታየው የመሬት ፖሊሲ የአንተን የአርሶ አደሩን መሠረታዊ ጥያቄ መመለስ ቀርቶ፤ እንዲያውም በተቃራኒው አንተን እየጎዳ የሚገኘው።

የአርሶ አደሩን መሠረታዊ የመሬት ጥያቄ በማያዳግም መልኩ ለመመለስ እንዲያስችል፤ ኢሕአፓ የራሱ የመሬት ፖሊሲ እንዳለው ተደጋግሞ የተገለጸ ነው። ሰማንያ አምስት ከመቶ ( 85 % ) የሚሆነው የሀገሪቱ ዜጋ በግብርና ተግባር የሚተዳደር በመሆኑ፤ የብሔራዊ ኢኮኖሚው ዓይነታ መሠረቱ እርሻ ነው። ስለሆነም፤ ከማንኛውም ብሔራዊ ፖሊሲ ባላነሰ መንገድ ለመሬት ፖሊሲ የሚሰጠው ክብደት ሚዛኑ የደፋ ይሆናል። የመሬትን ይዞታ ለመለወጥና የአርሶ አደሩን ህይወት ለማሻሻል ከተፈለገ፤ የአርሶ አደሩን መሠረታዊ ጥቅም ማዕከል ያደረገ የመሬት ፖሊሲ አውጥቶ በሥራ መተርጎም አማራጭ አይኖረውም። ይህም ማለት፤ መሬት ለአርሶ አደሩ፤ በግል ባለቤትነት ይዞታ በህግ ሊረጋገጥለት ይገባል ማለት ነው። የመሬት ፖሊሲው ደግሞ በእናውቅልሃለን በሚሉ ጥቂት ምርጦች ሳይሆን ሲቻለው በራሱ ካልተቻለውም እምነቱን በሚጥልባቸው ወኪሎቹ ሙሉ ተሳትፎ ሊቀየስ የሚገባው መሆኑ ደግሞ ከጥያቄ ሊገባ አይችልም። ለዚህም ነው ኢሕአፓ አርሶ አደሩ መሬቱን የማረስ ብቻ ሳይሆን፤ የመሸጥ- የመለወጥ፤ የማውረስ፤ በዋስትና/ በወለድ አግድ የማስያዝ፤ ሀገ መንግሥታዊ መብቱ ሊሆን ይገባል ተብሎ አፅንዖት

በተሞላበት ሁናቴ ሲገልጽ የቆየውና አሁንም እየገለጸ የሚገኘው። መሬት -አላባ የሆኑ አርሶ-አደሮችም፤ እንዲሁ በኅብረተሰቡ ስምምነትና ድጋፍ፤ የሚያርሱት መሬት በንብረትነት ማግኘት የዜግነት መብታቸው በመሆኑ፤ በህግ የተረጋገጠላቸው እንዲሆን አጥብቆ ሲታገል የቆየው።

የየካቲቱ 1966 ዓም አብዮት ካነሳቸው ሕዝባዊ ጥያቄዎች መካከል፤ የአርሶ አደሩ የመሬት ጥያቄ ( መሬት ለአራሹ ) ግንባር ቀደም መፈክር እንደነበረ ታሪክ መዝግቦታል ። ከ42 ዓመት በኋላ ይህ ጥያቄ አሁንም አልተመለሰም። በተወሰነ የታሪክ ወቅት ከሥልጣን በተቆናጠጡ ክፍሎች የገጠር መሬትን በሕዝብ ሥም በነሱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ማድረግም ከተመከሮ ለመገንዘብ እንደሚቻለውም የአርሶአደሩን ጥያቄና ፍላጎት ሊመልስ አይቻለውም፤ መፍትሄ ሊሆንም አይችልም። በመሆኑም የመሬት ጥያቄ አግባብነት ባለው ሁናቴ እስካልተመለሰ ድረስ ደግሞ ጎያው ሆኖ ይቀጥላል። የመሬት ጥያቄም ሆነ ሌሎች ሕዝባዊ ጥያቄዎች መነሻና መድረሻቸው ከዴሞክራሲ ጥያቄና ከነፃነት መብት መከበር ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። በሀገራችን የዴሞክራሲና የነፃነት ጥያቄዎች አሁንም መሠረታዊና ህያው ናቸው። በጎሳ ልዩነት ላይ በተመሰረተ ፖሊሲ በምትማቀቀው ኢትዮጵያ፤ ብሎም፤ የዴሞክራሲ ጭላንጭል እንኳ በማይታይባት ሀገር፤ የአርሶ አደሩን የመሬት ጥያቄ በተለይ ገንጥሎ ማየት አይቻልም። በኢትዮጵያ የመሬት ጥያቄን ለመመለስ እንዲቻል ተብሎ፤ የሥርዓት ለውጥ ማስፈለጉ፤ አንገብጋቢ ነበር። እናም የዐጼው ሥርዓት መለወጡ አይቀሬ ነበር ። ስለሆነም ሥርአቱ በሕዝባዊ አመፅ ተገረሰሰ፤ ተለወጠ። ለዚህም ነው ዛሬም እንደ ትላንቱ፤ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ችግሮች ለአንዴና ለመጨረሻው ለማስወገድ የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ ከነግሳንግሱ መለወጥ ግዴታና አንገብጋቢ ሆኖ የሚገኘው።

ውስብስብነቱ፤ በአያሌ ጥልፍልፍ ሀብሎች የተያያዘው የሀገራችን ሕዝብ ጎላዊ፤ በየፈርጁ እየታየ ሊፈታ የሚችልበት መፍትሄ ካልተገኘለት፤ ከዋናው ከተማ ላይ ቁጭ ተብሎ የሚታውጀው አዋጅ ብቻውን ችግሩን አይፈታውም። የሀገራችን አርሶ አደሮች መሠረታዊ ጥያቄዎች እስካሁን ደረስ መሠረታዊ መፍትሄ አላገኙም። ይኸም በመሆኑ፤ የአርሶ አደሩ ችግር አልተቃለለም። የገጠሩ ነዋሪም ከመካከለኛው ዘመን ያልተሻለ ህይወት ይመራል። ከዓመት እስከ ዓመት ቢያርስም እንኳን ቤተሰቡንና እራሱን በበቂ ሊመግብ አልተቻለውም። የጭሰኛና- ገባር ሥርዓት መወገድ በአውጅ ተሻረ ቢባልም፤ የመሬት ይዞታው ባለቤትነት ከፊውዳል መሬት ከበርቴዎች ከነበረው ወደ መንግሥት ባለቤትና ይዞታ ነው የተለወጠው። የጉልቻ መለዋወጥ እንደሚባለው የጌታ መዘዋወር፤ የአርሶ አደሩን ጥያቄ ሊመልሰው እንዳልቻለ ግልጽ ነው። አይችልምም። አርሶ አደሩ የራሱን መሬት በባለቤትነት መያዙን አረጋግጦ፤ የራሱን ምርት በራሱ ፋላጎትና ውሳኔ ገበያ እያወጣ፤ በኢኮኖሚ ህግ መሠረት፤ በአቅርቦትና - በፍላጎት ዝምድና እየተጠቀመ ካልተጠቀመ፤ መሬትን በመንግስት ስም መቀራመት ከችግሩ አያወጣውም። ከመሬት ተጠማኝነትም ነጻ

ሊያደርገው አይችልም። በወያኔ አገዛዝ አስጠማኝነት፤ በአርሶ አደሩ ተጠማኝነት ሆኖ የሚተዳደር ገበሬ ኑሮው፤ በርስተ- ጉልት ይዞታ ስር ከነበረው የፊውዳል ሥርዓት አገዛዝ እምብዛም አልተለወጠም ።

ከዚህ ሁሉ ያልተቋረጠ በደልና ስቃይ መገላገያህ ቀጥተኛ መንገድ አንድና አንድ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም በጫንቃህ ላይ የተጫነብህን፤ እራሱን የሰየመብህን የወያኔ አገዛዝ አሽቀንጥሮ መጣል ነው። ይህን ማድረግ እንዲያስችልህ ደግሞ እምቢ ብለህ በማመጽ መነሳትን ይጠይቃል። አመጽህን የተሳካ ለማድረግ፤ ይህን የማድረግ አቅም/ጉልበት ይኖርህ ዘንድ መደራጀትህና ባንድ ላይ ማበርህ የግድ ነው። አያቶችህ ድንበር ጥሰው የመጡ ወራሪዎችን ያንበረከኩት በሚስጥር በመቧደን፤ እምቢኝ አልገዛም ብለው በመሸፈት እንደሆነ የምታውቀው ነው፡፡

ዛሬም ተነስ፣ በቃኝን ልበስ፤ አጋርህ ከሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ጋር ሁሉ አብር። ባመቸህ መንገድ ሁሉ ተደራጅተህ እምቢታህን፣ ትግልህን አቀናጅ። በቤትህ፣ በቀየህ፣ ባካባቢህ ልብ ለልብ ከምትገናኘው ጋር ሁሉ የጭቆናው ዘመን የሚያከትምበትን ምከር። ሥርየት ካለ ደም አልመጣምና ነጻነትንም ካለ መስዋዕትነት አይዋጁም።

ኢሕአፓ ከዚህ ቀደም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የመገናኘት ዕድሉ በገጠመህ ቦታ ሁሉ አብሮህ ከጎንህ ተሰልፏል። በይፋም ይሁን በኅቡዕ ጭምር አደራጅቶ ሊያታግልህ የበኩሉን አስተዋጾ አድርጓል። አሁንም እንደትላንቱ ኢሕአፓ ቃል የሚገባልህ፤ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የጭቆናው ዘመን እንዲያከትም፣ ካንተ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ከጎንህ በመሰለፍ የሚጠየቀውን መስዋዕትነት ሁሉ እንደሚከፍል ነው። ኢሕአፓ ዛሬም "መሬት ለአራሹ"" ይሁን ይላል።

ኢሕአፓ ምንጊዜም የአርሶ አደሩና ባጠቃላይ የሥርቶ አደሩ ነው!

አርሶ አደሩ የነፃነቱና የሀገሩ(የመሬቱ) ባለቤትነቱ በትግሉ ይረጋገጣል!!

የአርሶ አደሩና ባጠቃላይ የሥርቶ አደሩ ትግል ያቸንፋል